# የስልጤ ዞን ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መምሪያ የሳይንስና ፈጠራ ስራዎች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

# የ2017 በጀት አመት እቅድ

**ግንቦት 2016**

**ዓ.ም**

**ወራቤ**

**መግቢያ**

የዞኑ መንግስት በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን ሀገራዊ ለውጥ ውጤታማ፣ ዘላቂና ተቋማዊ ለማድረግ እንዲሁም ከደረስንበት የዕድገት ደረጃ አንጻር የሚኖረውን ዘነዋ ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት የሚያስችል የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ስልጣንና ተግባር ፈትሾ ማስተካከል አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ቀደም ሲል የደቡብ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ኢንስቲትዩት ስር የነበረው የሳይንስ ቴክኖሎጂ ፈጠራ ስርፀት ዘርፍ ወደ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ  እንዲቀላቀል በማድረግ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መምሪያ በመባል በአዲስ መልኩ እንዲቋቋም የክልሉ ም/ቤት በቀን 08/02/2012 ዓ.ም ባካሄደው ጉባኤ የተሻሻለው የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 180/2012 ሆኖ መጽደቁ ይታወቃል፡፡

ስለሆነም ከዚህ ቀደም ሁለቱ ተቋማት ተጠሪነታቸው ለተለያዬ ሴክተር የነበረና የራሳቸው የሆነ ክልላዊ ተልዕኮአቸውን መወጣት የሚያስችላቸውን ዕቅድ አዘጋጅተው የሳይንስ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተግባርን ሲተገብሩ የቆዩ ቢሆኑም በሁለቱ ተቋማት በተበታተነ መልኩ ሲተገበር የቆየውን የሳይንስ፣ የኢኖቬሽን እና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተግባራትን በሃገራችን በፌደራል እና በአንዳንድ ክልሎች በተገኘ ተሞክሮ መነሻ ሁለቱ ተቋማት ተዋህደው በቢሮ ደረጃ እንዲቋቋም ከተደረገ ጀምሮ ጥረት ተሳክቶ የሳይንስ ኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ መምሪያ በመባል መቋቋሙ በዘርፉ ውጤታማ የሆነ ተግባርን ለማከናወን የተሻለ አቅም የሚፈጥር መሆኑ በመታመኑ ከዚህ ቀደም ብቻውን ከመጓዝ በመጣመር ለውጤታማነት በሚያበቃ መልኩ ይልቁንም በፊት ከነበረን የበለጠ ኃላፊነትን ያሸከመና ከወትሮ በተሻለ ፍጥነትና የአገልግሎት ጥራት መስራትን የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት የራስን አቅም አሟጦ በመጠቀምና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ያለንን ውስን የሆነውን በጀትና ማቴሪያል ወጪ ቆጣቢ በሆነ ዘዴ አብቃቅቶ በመጠቀም ላለቀ ውጤት የምንተጋበት የበጀት ዓመት እንደሚሆን ይታሰባል፡፡

በመሆኑም የስልጤ ዞን ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መምሪያ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት የሚያስችለውን የ2016  በጀት ዓመት የ12 ወር ዕቅድ አፈፃፀም መነሻ በማድረግ ይህ የ2017 ዓ.ም የቀጣይ የ12 ወራት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

# ክፍል-አንድ

## 1. የዳይሬክቶሬቱ ራዕይ ፣ ተልዕኮ ፣ ዓላማዎችና ዕሴቶች

### 1.1. ተልዕኮ

- ☞ የዞኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የሳይንስና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስራዎችን ለህብረተሰቡ በአግባቡ በማልማት፣ በመተግበርና በማስፋት ዞናዊ ክልላዊና ብሎም አገራዊ የተወዳዳሪነት አቅምና በቴክኖሎጂ የዳበረ የአሰራር ስርዓት መፍጠር ነዉ።

### 1.2. ራዕይ

- ☞ “በ2030 በዞናችን ውጤታማ የሆኑ የሳይንስና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት የመማር፣ የማልማት፤ የመፍጠር፣ የማላመድ እና የመጠቀም አቅም ተገንብቶ ማየት”

### 1.3. እሴቶች

- ☞ በጎ ህሊናና ቅን ልቦና፣
- ☞ የስራ ፍቅርና ትጋት፣
- ☞ ያልተገደበ አስተሳሰብና ምናባዊ ጉዞ፣
- ☞ ለለውጥ በጋራ መስራት፤
- ☞ ውጤታችንም ሆነ ውድቀታችን የጋራችን ነው፤
- ☞ ችግር ፈቺነት፤
- ☞ የማይረካ የመማር ጥማት፤
- ☞ ለትውልድ የሚተላለፍ መሠረት፣
- ☞ ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራርና ቀጣይነት ያለው መሻሻል፣

## 2. 2017 ዓ.ም የ12 ወር ዕቅዱን ለመፈጸም ያሉን ጥንካሬዎችና ድክመቶች እንዲሁም መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች/ SWOT Analysis/

### ሀ. ጥንካሬዎች /Strength

- በቡድን ወይም በቲም የመስራት ልምድና ፍላጎት መኖር
- በመምሪያዉ፤ በወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የዘርፉ ባለሙዎች የላቀ የስራ ተነሳሽነት መኖር
- ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የሚስችል የመገባቢያ ስምምነት ሰነድ በመፈራረም ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ
- ከግዜ ወደ ግዜ የሪፖርት አደራረግና የእቅድ አስተቃቀድ ግንዛቤዎች ከፍ ማታቸዉ
- ከክልል ጋር የነበረዉ ግንኙነት ከፍ ማለት መቻሉ

### ለ. ድክመቶች /Weakness

- የግብአት አቅርቦት እጥረት
- በክህሎት በቂ አቅም ያጎለበቱ ባለሙያዎች እጥረት መኖሩ
- የተጀመሩ የለውጥ ስራዎች ቀጣይነት አለመኖርና መቆራረጣቸው
- የስራ ሰዓት በትክክል አለመጠቀም
- በተለይ ሳይንስና ፈጠራ አከባቢ ተግባራት በመመሪያዎችና በማኑዋሎች አስደግፎ ከመሥራት አንጻር ውስንነት መኖሩ

### ሐ. መልካም አጋጣሚዎች /Opportunities

- የፈጠራ ፈጣሪዎች ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመሩ መምጣታቸዉና ለህብረተሰቡ ጠቃሚ ቴክኖሎጂዎችን መፍጠር መቻላቸዉ
- ቴክኖሎጂዎችን ከማስፋፋት አንጻር የተቋማት ፍላጎት እያደገ መምጣቱ፤
- በመምሪያዉ የበላይ አመራር መሟላትና ተግባራትን በፍላጎትና በቁርጠኝነት ለመምራት ያለው ተነሳሽነት መታየት መጀመሩ፤
- ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ልዩ የገበያ ተጠቃሚነት ደንብ መኖር
- ከዞን እስከ ወረዳና ከተማ አስተዳደር ድረስ ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀትና የሰዉ ሃይል መኖሩ፤

### መ. ስጋቶች /Threats

- የሰለጠኑና ልምድ ያላቸዉ ባለሙያዎች እጥረት
- በኢትዮ ቴሌኮም በኩል በመሰረተ ልማት ብልሽት ዙሪያ ፈጣን የጥገናና የማስተካከያ ስራ ያለመስራት የትብብር መንፈስ ክፍተት እና የኔትወርክ መቆራረጥ ችግር

- በዩኒቨርሲቲዎች የተደራጀ ኢንኩቤሽን ማዕከል አለመኖሩ
- በክልልም ሆነ በሰለጠኑ በለሙያዎች የስልጠናና የልምድ ልውውጥ አለመኖሩ፤
- ከወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች መረጃዎች በወቅቱ ያለመድረስ፤
- ክባትና የፈጠራ ስራዎችን ለመደገፍ የበጀት እጥረት መኖሩ፤
- ወደታች ወርዶ ስራዎችን ለመደገፍ የተሸከርካሪና ሞተር እጥረት መኖር

በአጠቃላይ በ2016 ዓ.ም በጠንካራና በደካማ ጎን የነበሩብን ውስንነቶችን ይዘን የዕቅድ አካል በማድረግ ለ2017 በጀት ዓመት የተቀመጡ ስጋቶችን ቀድመን በማወቅ የመልካም አጋጣሚዎች እንደ ግብዓት በመጠቀም እና ቀጣዩ በዕቅድ ዘመኑ ያልተፈጸሙትን ተግባራት በሚክስ መልኩ የዳበረ የአመቱ ዕቅድ በማዘጋጀት የየተግባሩን ዒላማ ለማሳካት ከወትሮው በተሻለ ሁኔታ የመፈጸም ወኔ ሰንቀን መገኘትና ይህንን የሚያረጋግጥ ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርብናል የሚል ስምምነት ላይ በመድረስ ከዚህ በታች ለሰፈረው ለቀሪው በጀት ዓመት ዕቅድ እንደ መነሽ ተወስዷል፡፡

### 3. የዕቅዱ ዋና ዓላማ

የዚህ ዕቅድ ዓላማ ዳይሬክቶሬቱ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ማለትም በዞኑ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የመዘርጋትንና የማስፋፋት ሥራዎችን በስትራቴጂያዊ አስተሳሰብ ለመምራት፣ በሁሉም ደረጃ ባሉ ፈጻሚዎች መካከል ተግባቦትን ፈጥሮ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ በበጀት ዓመቱ የታቀዱ ሥራዎችን ድጋፍ በመስጠት ዉጤታማ ማድረግ ነው፡፡

### 4. የዕቅዱ  አስፈላጊነት

- ዳይሬክቶሬቱ የተመረጠውን ትኩረት መስክና የተጣሉትን ስትራቴጂያዊ ግቦች በየደረጃው ያሉ ፈጻሚ አካላት በኃላፊነት ወስደዉ በባለቤትነት ስሜት እንዲሰሩና ውጤት ለማስመዝገብ የለውጥ ስራዎችን መደገፍ ፣
- በሁሉም ደረጃ የተቀናጀ የፕሮግራም ተግበራትን እውን ለማድረግ የሁሉም ፈጻሚ አካል አስተዋጽኦ አስፈላጊ በመሆኑ ተሳትፎአዊ አሠራርን ለማስፈን፣
- በደራሽ ሥራዎች የመጠመድን ችግር ለማስወገድና ስትራቴጂያዊ በሆነ አስተሳሰብ የዕቅድ አፈጻጸምን ለመምራትና ለእርምት እርምጃ አወሳሰድ ምቹ ሁኔታ ለመፈጠር ነው፡፡
- በተደራጀ መልኩ የዞኑን የክልሉንና የሀገርን ልማት ለማፋጠንና ዉጤት ለማምጣት

### 5. የዕቅዱ ወሰን

ይህ ዕቅድ ከሀምሌ 01/2016 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2017 ዓ.ም ባለው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ የሚከናወን የ ዕቅድ ሲሆን ዕቅዱ በየደረጃው ላሉ ዳሬክቶር ፈጻሚ አካላት በማውረድ የሚከናወን ሆኖ ይኼውም ፣ በዞንመምርየዉ ዳይሬክቶሬት ፣ በወረዳና በከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቶች የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬቶችና አስፈጻሚ አካላት የሚከናወን ይሆናል፡፡

# ክፍል-ሁለት

## 2. ከአበይት ተግባራት አንፃር

**የተቋሙ የልማት ስራዎችን ለማሳለጥ የተጣሉ ግቦችና በግቦቹ ስር የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን በተመለከተ**

1. **ምቹ የምርምርና የፈጠራ ስራ ምህዳር በመፍጠር የተመራማሪዎችንና የፈጠራ ባለሙያዎችን ውጤታማነት ማሳደግ**
    - የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ከፍ ለማድረግ 01 የምክክር መድረክ ማዘጋጀት
    - በዙር አንድ ጊዜ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ፓናል ውይይት ማዘጋጀት
    - ለኢኖቬሽን ስራዎች ድጋፍ አገልግሎት በጀት በማፈላለግ 08 ፕሮጀክትቶችን በገንዘብ መደገፍ
    - በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ክበባት ለሚሰሩ 03 የፈጠራ ስራዎች የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ አቅማቸውን ማሳደግ
    - አንድ ዙር የፈጠራ ስራዎችን ዉድድርና ሽልማት ስነስርአት በወረዳዎችና በዞን ደረጃ ማካሄድ
    - የአከባቢዉን ህብረተሰብ መጥቀም የሚችሉ በጥናትና ምርምር የተለዩ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል 02 ቴክኖሎጂዎችን ናሙና በማምረት ፈትሾ በማሸጋገር የአከባቢዉን ህብረተሰብ እንዲጠቀም ማድረግ፡፡
2. **ብቁና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማትን መፍጠር**
    - በዞኑ ዉስጥ ካሉት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለተቋቋሙ  የሳይንስና ቴክኖሎጂ ክበባት ቢያንስ 04 ክበባትን  በቁሳቁስ በመደገፍ አቅማቹን እንዲያሳድጉ ማድረግ
3. **ውጤታማ የትብብር ስርአትን ማረጋገጥአንፃር**
    - ለ10 ወረዳዎችና ፣ 05 ከተማ አስተዳደሮች እና ስራው ለሚመለከታችው አካላት በአዕምሯዊ ንብርት ጥበቃና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ዙሪያ 01 ዙር ግንዛቤ የማስጨበጥ ስልጠና መስጠት
    - የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ለመስጠት የፈጠራ ስራዎች አዲስነት ለመለየት 01 የጥናት ሰነድ ማዘጋጀት

4. **ምቹ የስራ አካባቢን መፍጠርና የሰው ሃብት ውጤታማነትን ማሳደግ**

- የዞን መምሪያ ወደታችኛው መዋቅር ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ላይ በስራ ሂደት በመዉረድ ቴክኒካል ድጋፍና ክትትል 02 ዙር ማድረግ
- የዞን መምሪያ ወደታችኛው ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች መዋቅር በየሩብ አመቱ መደበኛ ድጋፍና ክትትል 04 ዙር ማድረግ

5. **የጨረር አመንጪ መሳሪዎች አጠቃቀም ችግሮችን በመከላከል የህብረተሰቡን ደህንነት ከማረጋገጥ ረገድ**

- በዞን ደረጃ፤ በወረዳ ደረጃና በከተማ አስተዳደር ደረጃ ከሚገኙ የመንግስትም ሆነ የግልየጤና ተቋማት የሚገኙ የጨረር አመንጪ መሳሪያዎችን 01 ዙር መረጃ በማጠናከር ለሚመለከተዉ አካል መላክ

| የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ መላኪያ ቴምፕሌት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የ2017 በጀት ዓመት ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የ2016 መነሻ | የ 2017 ዓ.ም ዕቅድ ዒላማ | ምርመራ |
| | | | | | |
| ግብ.1 ምቹ የምርምርና የፈጠራ ስራ ምህዳር በመፍጠር የተመራማሪዎችንና የፈጠራ ባለሙያዎችን ውጤታማነት ማሳደግ | | | | | |
| 2.2. | በዙር አንድ ጊዜ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ፓናል ውይይት ማዘጋጀት | በዙር | 01 | 01 | |
| 2.3 | ለኢኖቬሽን ስራዎች ድጋፍ አገልግሎት በጀት በማፈላለግ 08 ፕሮጀክትቶችን በገንዘብ መደገፍ | በቁጥር | - | 08 | |
| 2.4 | በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ክበባት ለሚሰሩ 03 የፈጠራ ስራዎች የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ አቅማቸውን ማሳደግ | በዙር | - | 02 | |
| 2.5 | የሳይንስ ና ቴክኖሎጂ ሳምንታትን ለማክበር ተለይተውግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የወሰዱ ት/ቤቶች | በቁጥር | 07 | 07 | |
| 2.6 | የሳይንስናቴክኖሎጂ ሳምንታት የተከበረባቸው ት/ቤቶች ማሳደግ | በቁጥር | 06 | 07 | |
| 2.7 | አንድ ዙር የፈጠራ ስራዎችን ዉድድርና ሽልማት ስነስርአት በወረዳዎችና በዞን ደረጃ ማካሄድ | በዙር | 01 | 01 | |
| 2.8 | አከባቢውን የልማት አቅም መሰረት ያደረግ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም የምርት ብክነትን ለመቀነስ የሚያስችል (ግብርና ላይ) 03 የሳይንስ ቴክኖሎጂ ምርምርና ጥናት ስራዎችን ማካሄድ፣ | በቁጥር | 1 | 03 | |
| 2.9 | የአከባዉን ህብረተሰብ መጥቀም የሚችሉ በጥናትና ምርምር የተለዩ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል 02 ቴክኖሎጂዎችን ናሙና በማምረት ፈትሾ በማሸጋገር የአከባዉን ህብረተሰብ እንዲጠቀም ማድረግ። | በቁጥር | - | 02 | |
| 2.10 | የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ከፍ ለማድረግ 01 የምክክር መድረክ ማዘጋጀት | በቁጥር | 01 | 01 | |
| ግብ.3. ብቁና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማትን መፍጠር | | | | | |
| 3.4 | በዞን ዉስጥ ካሉት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተቋቋሙ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ክበባትን ቢያንስ ለሶስት የተቋቋሙትን ክበባት በቁሳቁስ ድጋፈ በማድረግ አቅማቸዉን ማሳደግ | በቁጥር | - | 02 | |
| ግብ.4. ውጤታማ የትብብር ስርአትን ማረጋገጥ | | | | | |
| 4.5 | ለወረዳናበከተማ አስተዳደር እና ስራው ለሚመለከታቸው አካላት በአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ዙሪያ ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ ማስጨበጥ | በዙር | 01 | 01 | |
| ግብ 5. ምቹ የስራ አካባቢን መፍጠርና የሰው ሃብት ውጤታማነትን ማሳደግ | | | | | |
| 5.8 | የዞን መምሪያ ወደታችኛው መዋቅር ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ላይ በስራ ሂደት በመዉረድ ቴክኒካል ድጋፍና ክትትል 02 ዙር ማድረግ | በፐርሰንት | - | 02 | |
| 6. ግብ.12 የጨረር አመንጪ መሳሪዎች አጠቃቀም ችግሮችን በመከላከል የህብረተሰቡን ደህንነት ማረጋገጥ | | | | | |

| የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ መላኪያ ቴምፕሌት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የ2017 በጀት ዓመት ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የ2016 መነሻ | የ 2017 ዓ.ም ዕቅድ ዒላማ | ምርመራ |
| 13.1 | ከቤሔራዊ የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ መ/ቤት ጋር ጠንካራ ትስስር መፍጠር፣ | በቁጥር | - | 1 | |
| 13.2 | በዞን ደረጃ፤ በወረዳ ደረጃና በከተማ አስተዳደር ደረጃ ከሚገኙ የጤና ተቋማት የሚገኙ የጨረር አመንጪ መሳሪያዎችን 01 ዙር መረጃ በማጠናከር ለሚመለከተዉ አካል መላክ | በዙር | - | 01 | |
| ግብ.13 ቀልጣፋና አስተማማኝ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ስርጭትን ማረጋገጥ | | | | | |
| 15.10 | 2 ዙር በወረዳዎችና በከተማ አስተዳደሮች በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ በመስክ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሪፖርት እና ግብረ መልስ ማዘጋጀት፣ | በዙር | 02 | 02 | |

# ክፍል ሶስት

**የአፈፃፀም ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና እና ግብረ-መልስ ሥርዓት**

**የ**ዕቅድ ትግበራ ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማ እና ምዘና ሥራዎች ከዚህ በታች በተመለከተው ሁኔታ ይከናወናሉ፡፡

**የአፈጻጸም ስልት**

የተለዩትን የትኩረት መስኮች በተቀላጠፈና በተሳካ ሁኔታ ወደ ተጠቀሱት ግቦች ለማሸጋገር የሚከተሉት የአፈጻጸም ስልቶች ተለይተዋል፡፡

- ከባለድርሻ አካላትና ከዞን መስሪያ ቤቱ ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችል ግንኙነት መፍጠር፣
- የዘርፉ ስራዎች ውጤታማ ሊያደርጉ የሚያስችሉ የተለያዩ ልምድ ልውውጦችን ማድረግ፡፡

**የአፈፃፀም ክትትል**

በዕቅድ ትግበራው ፈፃሚ አካላት ለተገልጋይ ደንበኞች ተጨማሪ እሴትና እርካታን መፍጠር የሚያስችል የውስጥ አሰራር ሥርዓት መዘርጋትና እርካታን ማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ አቅማቸውን ማጎልበት እንዲችሉ ተከታታይና ወቅታዊ የሆነ የድጋፍና ክትትል ሥራዎች ማካሄድ ተገቢ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የክትትል ተግባሩ የዕቅድ ትግበራ መከታተያ ቅጾችን በመጠቀም፣ ለአገልግሎት መስጫ፣ ለክትትልና የመረጃ አሰባሰብ የተዘጋጁ ሌሎች ቅፆችን በመጠቀም፣ የዕቅድ አተገባበሩን በአካል ተገኝቶ በማየት፣ በየጊዜው በሚደረገው ሪፖርቶች የተገልጋይ አስተያቶችን በማሰባሰብ ፣ በማደራጀትና በመተንተን፣ የተገልጋዮችና የባለድርሻ አካላት በውይይት መድረኮች በሚያነሷቸው ሀሳቦች በግብዓትነት መጠቀም ይገባል፡፡

**ድጋፍ ማድረግና ማማከር**

በአፈጻጸም ክትትል የሚታዩ ክፍተቶችን መሠረት በማድረግ ለዕቅዱ ትግበራ ስኬታማነት በየደረጃው ላሉ ፈፃሚዎች የዕቅድ አፈፃፀም ብቃት እንዲጎለብትና የወደፊት የሥራ አፈፃፀማቸውን ማሻሻል በሚያስችል መልኩ ድጋፍና የማማከር ተግባራት የሚከናወን ይሆናል፡፡

**የአፈፃፀም ግምገማ**

በዘርፉ የሚካሔዱ ግምገማዎች መሻሻል የሚገባቸውን ችግሮች ለመለየትና ሊወሰዱ የሚገባቸውን የማሻሻያ እርምጃዎች መጠቆም በሚያስችል መልኩ የሚከናወኑ ሲሆን ዘዴዎች ዕቅድን ከአፈፃፀም ጋር በማመሳከር፣ ከዕቅዱ በፊትና በኋላ የተስተዋሉ ለውጦችን በመገምገም፣ ከአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በየጊዜው ተሰብስበ ምክክር በማድረግ፣ ተደራጅቶና ተተንትኖ የተዘጋጀውን የተገልጋይ ዳሰሳ ጥናት ውጤት መሠረት በማድረግ፣ በክትትል ወቅት የተጠናቀሩ መረጃዎችን በመመርመር እና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በመፈተሽ ይሆናል፡፡

**ግብረ መልስ**

በዘርፉ ፈጻሚዎች ዕቅዳቸውን እየፈጸሙ የሚገኙበትን አግባብ መሠረት በማድረግና ግቦችና ዒላማዎችን ከሚጠበቀው ውጤት አንጻር በመለካት የተሳኩና ያልተሳኩትን ለይቶ በማመላከት ምላሽ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

**ማጠቃለያ**

በበጀት ዓመቱ ለማከናወን የተጣሉ ግቦች መሳካት እንዲችሉ የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ሰጥተው አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በዚሁ መሠረት ተግባሩን በተገቢ መልኩ ማከናወን ይችል ዘንድ አስፈላጊውን አደረጃጀት በፍጥነት በመፍጠር መጠነ ሰፊ የሆነውን የህብረተሰብ የልማት ፍላጎት መመለስ የሚያሥችል አቅም ስርዓት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡